# ‹‹ኤፈርት መር ካፒታሊዝም›› የዘራፊዎች ካፒታሊዝም በመሆኑ አጥብቅን እንዋጋዋለን።

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 57 ርዕሰ አንቅጽ

የወያኔ የተውገረገረ የኢኮኖሚ ፓሊሲ ምንነት እንደሰሞኑ የአቶ ስብሃት ነጋ ቃለ-መጠይቅ ይፋ ያወጣ የለም። አቶ ስብሃት የድርጅታቸው የኢኮኖሚ ፓሊሲ ግብ ካፒታሊዝም መሆኑን ነገሩን። ይህ አባባላቸው የአፍ ወለምታ ሳይሆን ተዘጋጅተው እንደመጡበት ‹‹ካፒታሊዝም›› የሚለውን ቃል ከሚገባው በላይ በመደጋገም አረጋገጡልን። ኤፈርት ለካፒታሊዝም በኢትዮጵያ እውን መሆን እንደሚተጋም ተከራከሩ። ቀጥለውም የካፒታሊስቱ መደብ ሲጎለብት ኢህአዴግ ስልጣኑን አስረክቦ እንደሚከስም ቃል ገቡ።

በወያኔዎች ‹‹አቦይ›› እየተባሉ የሚቆላመጡት ስብሃት ነጋ ከዚህም በላይ ብዙ የዘባረቁ ቢሆንም ለጊዜው በእነዚህ ላይ ብቻ እናተኩራለን።

ለመሆኑ ስብሃት ነጋ በግል፣ ወያኔ እንደ ቡድን ካፒታሊዝምን ያውቁታል? ስለ ካፒታሊዝም ብዙ እጅግ ብዙ የተባለና ወደፊትም ብዙ የሚባል ቢሆንም ቢያንስ የሚከተሉት ሶስት ነጥቦች መሠረታዊ ናቸው።

1. ካፒታሊዝም በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ነው። ለዚህም ነው ካፒታሊዝምና ዲሞክራሲን ነጣጥሎ ማየት አስቸጋሪም አሳሳችም ነው የሚባለው።
2. የካፒታሊዝም መሠረቱ የግል ሃብት ነው። በካፒታሊዝም መንግሥት በኢኮኖሚ ላይ ያለው ተሳትፎ ፍትሃዊ ፓሊሲዎችን በማውጣትና በማስፈፀም ላይ የተወሰነ ሲሆን፣ መንግሥት በገበያ ውስጥ ጣልቃ የሚገባው ከግሉ ኢኮኖሚ በተሻለ ይሰራቸዋል በሚባሉ ተግባራትና ጊዜዓት ብቻ ነው።
3. በካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሥልጣን እና የፓለቲካ ሥልጣን የተለያዩ ናቸው። ሃያማኖትና መንግሥት እንደተለያዩ ሁሉ ገንዘብና የመንግሥት ሥልጣንም የተለያዩ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩት ሶስት መሠረታዊ ነገሮች ያልያዘ ሥርዓት ካፒታሊስታዊ ነው ሊባል አይችልም።

የወያኔ ካፒታሊዝም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ለአንዳቸውም ደንታ የለውም። በወያኔ ሊገነባ የታቀደው ካፒታሊዝም ነፃነትን ሳይሆን ባርነትና ዘረፋን መሠረት ያደረገ ነው። እንዲያውም በጭንቅላታቸው ያለው ካፒታሊዝም ሳይሆን ኢምፔሪያሊዝምን ይመስላል። ‹‹ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም›› ብዙዎችን እያደኸየ ጥቂት የወያኔ ጎጠኞ ገገሮችን ግን በሃብት እያንበሻበሸ መሆኑ እና ወያኔ ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው በወረራ እንደያዛት አገር የመሆኑ እውነታ እየገነቡት ያለው የኢኮኖሚ ሥርዓትን እነሱ ‹‹ካፒታሊዝም›› ብለው ቢጠሩትም ከካፒታሊዝም ይልቅ ለኢምፔሪያሊዝም ይቀርባል። ‹‹ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝም ከፍተኛውና የመጨረሻው ደረጃ ነው›› የሚለው ሌሊናዊ ቀኖና ለወቅቱ ሁኔታ ሲያስማሙት ‹‹ካፒታሊዝም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ከፍተኛውና የመጨረሻ ደረጃ ነው›› ወደሚል አስቂኝ መደምደሚያ እንደደረሱ ልብ ይሏል።

ለወያኔዎች ካፒታሊዝም ማለት ጥቂት ሃብታሞች ያሉበት ሥርዓት ማለት ሲሆን፤ የሚሊኒየሮች መኖር ደግሞ ለካፒታሊዝም መገንባት ማረጋገጫ ነው። አቶ ስብሃት አይናገሩት እንጂ የጦር መኮንኖቻቸውና ባለሥልጣኖቻቸው በጥቂት ዓመታት ውስጥ ባለብዙ ሚሊዮኖች መሆን የካፒታሊዝም ውጤት አድርገው ይወስዱታል። ወያኔ የዛሬ ዓመት ግድም ሚሊየነር ስለሆኑ ገበሬዎች መፈጠር ነግሮን ነበር፤ አሁን ያ ወሬ ሲነፍስበት በኤፈርት ተኩልን።

ለመሆኑ ኤፈርት ምንድነው? የማነው? የአቶ ስብሃትን ማጭበርበሪያ ወዲያ ጥለን ኤፈርት ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ምን ማለት እንደሆነ ባጭሩ እንግለጽ።

ኤፈርት /በትግርኛው ምህፃር ‹‹ትእምት››/ ወያኔ በረሃ እያለ ባንኮችን፣ የመንግሥት መኪናዎችን እና የግለሰቦችን ንብረት በመዝረፍ ያቋቋመው ህገ-ወጥ የዘራፊዎች ድርጅት ነው።

ወያኔ የሚኒሊክ ቤተመንግስትን ከተቆጣጠረ ወዲህም ኤፈርት ራሱን በአስራ ሶስት ግዙፍ ኩባንያዎች አደራጅቶ በሁሉም አቅጣጫ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በመቦጥቦጥ የወያኔ ሹማምንትን ኪስ እንዲያደልብ አደራ ተጥሎበታል። በዚህም መሠረት መሶበ የኮንስትራክሽን ግብዓት ማምረቻ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ፣ አዲስ የመድሃኒት ማምረቻ፣ ኢዛና የማዕድን ልማት፣ ጉና የንግድ ድርጅት፣ ሕይወት የግብርና ሜካናይዜሽን፣ ሳባ እብነ በረድ ማምረቻ፣ ሼባ የቆርቆሮ ፋብሪካ፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ አልሜዳ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ኤክስፕረስ የትራንዚት አገልግሎት፣ ኢትዮጵያን እንወቅ አስጎብኚ ድርጅት እና ትራንስ ኢትዮጵያ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት የተሰኙ ግዛዙፍ ኩባንያዎችን አቋቁሞ አቶ ስብሃት እንዳሉትም በመላው ኢትዮጵያ ተንሰራፍቷል።

ይህም አልበቃ ብሎ በቅርቡ ደግሞ ብሩህ ተስፋ ፕላስቲክ ፋብሪካ፣ ማይጨው ፓርቲክል ቦርድ ፋብሪካ፣ ዲማ የማር ማጣሪያ፣ አላጌ ደንና የደን ውጤቶች፣ ናሽናል ጂኦ-ቴክስታይል እና አበርደሌ የእንስሳት ማድለቢያና ኢክስፖርት ድርጅት የተባሉ ስድስት ኩባንያዎች የያዘው ደጀና ኢንዳውመንት ተጨምሮለት የበለጠ እንዲንሰራፋ ከተደረገ በኋላ አዜብ መስፍን በቅርበት እንትቆጣጠረው በም/ሥራ አስኪያጅነት ተመድባለች።

ከላይ የተዘረዘረው ኤፈርት በአደባባይ የሚሰራውን ነው። የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በቅርበት የሚከታተሉ እንደሚያውቁት ሁሉ ኤፈርት በኮንትሮባንድ ንግድ ጭምር የገባ ከመሆኑም በላይ ያሻውን ያህል ተበድሮ ያለመክፈል ልዩ ፈቃድ ያለው ቅምጥል ድርጅት ነው። ለማስረጃም ያህል ብዙ ድርጅቶች በባንክ እዳ በሃራጅ ሲሸጡ ለኤፈርት ግን ከሶስት ቢሊዮን በላይ የባንክ እዳ ተዘርዞለታል። እንዲያም ሆኖ ኤፈርት የጌቶቹን ኪስ በመሙላት እንጂ በአትራፊነቱ እጅግም የሚታወቅ ድርጅት አይደለም። ባጭሩ ኤፈርት ኢትዮጵያን በመዝረፍ ተቋቁሞ አሁንም በመዝረፍ ላይ ያለ የወያኔዎች የማይሞላ ቀዳዳ ኮሮጆ ነው።

የወያኔ የኢኮኖሚ ፓሊሲ ቀድሞ ይታወቅበት ከነበረው ‹‹ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት›› ወደ ‹‹ኤፈርት መር ካፒታሊዝም›› መሸጋገሩን አቶ ስብሃት ሲገልፁልን የሚያልሙት ካፒታሊዝም ‹‹የዘራፊዎች ካፒታሊዝም›› ስለመሆኑ ከራሱ ከኤፈርት ሌላ ዋቢ አያሻም።

በኤፈርትም ሆነ ሌሎች መሰል ኩባንያዎች ሽፋን እተደረገ ያለው ዘረፋ ማስቆም የዚህ ትውልድ ግዴታ ነው። ኤፈርት መር ካፒታሊዝም የሽፍቶች ካፒታሊዝም በመሆኑ አጥብቅን እንዋጋዋለን።

http://www.ginbot7.org/News_Paper/Ginbot_7_Dimts_Issue_No57.pdf